# ኤምፔሳ ዕቁብ ደንብና ሁኔታዎች

**መቅድም**

ዕቁብ የኢትዮጵያ ባህላዊ ገንዘብ ማሰባሰቢያና የተሰበሰበው ገንዘብ በየተራ ለአባላት የሚከፋፈልበት ዘዴ ነው። ሳፋሪኮም ኤምፔሳ ሞባይል የፋይናንስ አገልግሎቶች ኃ/የተ/የግል ማኅበር (ሳፋሪኮም ኤምፔሳ) የተፈቀደለት የፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ እንደመሆኑ በኤምፔሳ መተግበሪያ ሥርዓቱ ሥር ይህንን በየተራ የተሰበሰበ ገንዘብ የሚከፋፈልበትን ዘዴ ለማገዝና ለማሳለጥ የሚያስችል ዲጂታል መፍትሔ አቅርቧል። ይህ በዲጂታል መንገድ የሚሰበሰበው መዋጮ በመላው ኢትዮጵያ የኤምፔሳን መተግበሪያ በመጠቀም ደንበኛው በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በሞባይል ስልካቸው ገንዘብ እንዲሰበስቡ ያስችላቸዋል።

1. **ትርጓሜ:**

   በዚህ ስምምነት ላይ ዓውዱ በሌላ መልኩ እንዲገለጽ ካላስገደደ በቀር የሚከተሉት ቃላትና አባባሎች የሚከተለው ትርጓሜ ይኖራቸዋል፡-

   **1.1** «የዕቁብ አካውንት» በእርስዎ ጥያቄ መሠረት በሳፋሪኮም ኤምፔሳ የሚከፈት ሒሳብ ሆኖ ዓላማውም ከተለያዩ ምንጮች ገንዘብ ማሰባሰብ እንዲቻል ሲሆን ይህ አካውንት የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜ ካለው ከእርስዎ የኤምፔሳ አካውንት ላይ ተጨማሪ አካውንት ነው፤ በዕቁብ አካውንት ወይም በዕቁብ ቁጥር ላይ የሚኖርን ጥርጣሬ ለማስወገድ እንዲረዳ ሁለቱም የሳፋሪኮም ኤምፔሳ እና የሳፋሪኮም ኤምፔሳ ንብረት ሆነው እንደሚቀሩ እናሳስባለን።

   **1.2** «ደንበኛ» ማለት በደንበኛው የዕቁብ ሒሳብ ተጠቅሞ ቡድን ለመፍጠር ወይም ገንዘብ ለመክፈል/መዋጮ ለማዋጣት የኤምፔሳን ሲስተም የሚጠቀም የኤምፔሳ ተጠቃሚ ነው።

   **1.3** «ቡድን» ወይም «የኤምፔሳ ዕቁብ ቡድን» ማለት በመካከላቸው እና በተመሳሳይ ቡድን ውስጥ ባሉ በሁሉም የኤምፔሳ ደንበኞች/አባላት መካከል ገንዘብ ለመካፈል ዓላማ በኤምፔሳ ሲስተም ውስጥ የዕቁብ አገልግሎትን ለመጠቀም ቡድን የሚፈጥሩ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የኤምፔሳ ደንበኞች/አባላት ናቸው።

   **1.4** «አደራጅ» ማለት በኤምፔሳ ላይ የዕቁብ ቡድንን የሚፈጥረው፣ ወደ ቡድኑ አባላትን የሚጋብዘው እና ከሌሎች የዕቁቡ የቡድን አባላት ጋር በመስማማት የቡድኑን ሕግ የሚያስቀምጠው የዕቁብ ተጠቃሚ ነው። አደራጅ ወዲያውኑ ከቡድኑ ፈቃድ ሰጪዎች መካከል አንዱ ይሆናል።

   **1.5** «ፈቃድ ሰጪ» ወይም «ፈቃድ ሰጪዎች» የቡድኑን ክንውኖች በበላይነት ከሚመሩት ሁለት አስተዳዳሪዎች መካከል አንዳቸው ማለት ሲሆን የገንዘብ ዝውውር እንዲከናወን ፈቃድ እንዲሰጡ፣ ክፍያዎችን እንዲፈጽሙ፣ የቡድን አባላትን ሚና እንዲቀይሩ፣ (ቡድኑ ዕጣ የሚወጣበትን ቅደም ተከተል አስቀድሞ የሚወስን ከሆነ) አባሉ ዕጣ የሚወጣለትን ቅደም ተከተል እንዲለውጡ እና ቡድኑ እንዲዘጋ ለመጠየቅ ሥልጣን አለው ወይም አላቸው። ፈቃድ ሰጪዎች በሌሎች ፈቃድ ሰጪዎች የተጀመሩ የገንዘብ ዝውውሮችን ማጽደቅ ይችላሉ።

2. **ስምምነቱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ**

**2.1** እነዚህ ደንቦችና ሁኔታዎች የዕቁብ ቡድኑ እና ዋሌት በሥራ ላይ በሚቆይበት ጊዜ ላይ ተፈጻሚ እንደሆኑ ይቆያሉ። ሁሉም የዕቁብ ዋሌቶች በደንበኞች ፍላጎት መሠረት የተወሰነ ፀንተው የሚቆዩበት የራሳቸው ውስን ጊዜ ይኖራቸዋል። አንድ የዕቁብ ቡድን ቡድኑ ሲቋቋም እንዲወጡ የታሰቡት ዕጣዎች በሙሉ ወጥተው ሲያልቁ ወዲያውኑ ይዘጋል።

**2.2** የዕቁብ ቡድን ፈቃድ ሰጪዎች በአንድ ፈቃድ ሰጪ ቡድኑ እንዲዘጋ ጥያቄ ከቀረበ እና በተደነገገው የፈቃድ ሰጪዎች ብዛት ልክ ጥያቄው ተቀባይነት ካገኘ ቡድኑን ሊዘጉት ይችላሉ።

**2.3** የዕቁብ ቡድኑን የቆይታ ጊዜ እንዲራዘም የማድረግ ዕድል አልዎት ወይም ማራዘሚያ ጥያቄው ተቀባይነት ካላገኘ አገልግሎቱ ስለሚቋረጥበት ጊዜ ማስታወቂያ እንዲደርስዎት ይደረጋል።

**2.4** ሳፋሪኮም ኤምፔሳ አገልግሎቱ በሚራዘምበት ጊዜ እና/ወይም አካውንቱ በሚዘጋበት ሂደት ላይ በእርስዎ ላይ ለሚደርስ ኪሣራ ምንም ዓይነት ኃላፊነት የማይወስድ እና ካሣ የማይከፍልዎት ስለሆነ የአገልግሎት ጊዜው በሚያበቃበት ጊዜ የዕቁብ አካውንቱ ምንም ቀሪ ሒሳብ በላዩ ላይ ያልቀረ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለብዎት።

## 3. የዕቁብ አካውንቱን ሥራ ማስጀመር

**3.1** ልክ የዕቁብ አካውንቱ በሳፋሪኮም ኤምፔሳ ደንበኛ ሥራ እንዲጀመር ሲደረግ እና/ወይም ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቅም ላይ ሲውል ይህ ስምምነት ተፈጻሚ ይሆናል፤ በዚህም መሠረት እርስዎ የኤምፔሳን የሥራ ክንውን መመሪያዎች፣ የደንበኛ

**3.1.1** ደንብና ሁኔታዎች እና ከጊዜ ወደ ጊዜ በሳፋሪኮም ኤምፔሳ በነዚህ ደንቦችና ሁኔታዎች ላይ ለውጥ ሊያደርግ እንደሚችል እንደሚያውቁ፣ አንብበው እንደተረዱ፣

**3.1.2** በደንብና ሁኔታዎቹ ለመገዛት እንደተስማሙ እና

**3.1.3** ባዮሜትሪክ ምዝገባን ጨምሮ ማናቸውንም ደንበኛውን ለይቶ ለማወቅ አስፈላጊ የሆኑ የምዝገባ ሂደቶችን በሙሉ እንዳሟሉ ያረጋግጣሉ።

## 4. የሥራ ክንውን እና የስምምነቱ አድማስ

**4.1** መዋጮ አድራጊዎች በቀጥታ ከኤምፔሳ አካውንታቸው መዋጮ መፈጸም እንዲችሉ ኤምፔሳ ዕቁብ አገልግሎት በኤምፔሳ ዋሌቶች (የዕቁብ አካውንት) ውስጥ በተለየ የመዋጮ ዋሌት ላይ እንዲመዘገቡ ያስችላቸዋል።

**4.2** በኤምፔሳ፣ በዩኤስኤስዲ ኮድ 733# ወይም በኤምፔሳ መተግበሪያ ውስጥ ባለው የፋይናንስ አገልግሎቶች ማውጫ በኩል የሳፋሪኮም ኤምፔሳ ደንበኞች የኤምፔሳ ዕቁብ ቡድኖችን መፍጠር እና ሌሎች የኤምፔሳ ደንበኖችን አባል እንዲሆኑ ግብዣ መላክ ይችላሉ።

**4.3** ቡድን በሚፈጥርበት ጊዜ አደራጁ የቡድኑን ስም፣ የቡድኑን አባላት ብዛት፣ የመዋጮ መጠን፣ አንድን የገንዘብ ዝውውር ለማጽደቅ የሚያስፈልጉት ፈቃዶች ብዛት፣ ቡድኑ ክፍያ የሚፈጽምበት ዙር ወይም መዋጮ የሚደረግበት ጊዜ ገደብ እና የአከፋፈል ዓይነት (በዕጣ፣ በቅደም ተከተል ወይም በትዕዛዝ) እንዲያስገባ ይደረጋል።

**4.4** የቡድን አደራጁ በተጨማሪ ወደ ቡድኑ የሚጋብዘውን የቡድን አባል መወሰን፣ የቡድኑን አባላት ሚና መለየት (ፈቃድ ሰጪ ወይም ተራ አባል)፣ የሚጠበቀው የመዋጮ ገንዘብ መጠን እና (ቡድኑ በቅደም ተከተል ክፍያ ለመፈጸም ከመረጠ) የክፍያ አፈጻጸሙን ቅደም ተከተል መወሰን ይችላል።

**4.5** የቡድን አደራጁ አባላትን ማሰናበት፣ የክፍያ ቅደም ተከተሉን መቀየር፣ የቡድን አባላትን ሚና መለወጥ፣ እና ቡድኑን መዝጋት ይችላል።

**4.6** ከስምምነት ላይ በተደረሰበት ጊዜ እና የገንዘብ መጠን መዋጮውን ሳይከፍሉ መቅረት ሌሎች የዕቁብ ቡድኖችን እንዳይቀላቀሉ መታገድ ወይም ደንበኛው ከዚህ ቀደም አባል ከሆነባቸው ቡድኖች የሚወጣለትን ዕቁብ ክፍያ እንዳይቀበል መደረግን ጨምሮ የሚያገኙት የኤምፔሳ አገልግሎቶች ላይ ገደብ እንዲጣል ወይም እንዲታገዱ ሊያስደርግ ይችላል።

**4.7** ስምምነቱ ተፈጻሚ ከሚሆንበት ቀን ጀምሮ ስምምነቱ ተፈጻሚ ሆኖ እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ ሳፋሪኮም ኤምፔሳ የሚከተሉትን ያደርጋል፡-

**4.7.1** ከመደበኛው የእርስዎ የኤምፔሳ አካውንት የተለየ የዕቁብ አካውንት(ቶች) የሚሰጥዎት ሲሆን በዚህም አካውንት ደንበኞች (ለምሳሌ የእርስዎ ዕቁብተኞች) በደንበኛ የኤምፔሳ ማውጫ በኩል ተገቢነት ባለው የዕቁብ አገልግሎት ተጠቅመው ለዕቁብ ኤምፔሳ አካውንታቸው መዋጮ ማዋጣት ይችላሉ።

**4.7.2** ደንበኛው ሁለቱንም የኤምፔሳ አካውንት እና የዕቁብ አካውንት(ቶች) ሊያስተዳድር የሚችልበትን የኤምፔሳ ማውጫ መጠቀም እንዲችል የሚያደርግ ለደኅንነት አስተማማኝ የሆነ መዳረሻን ይሰጣል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ የእርስዎን የምስጢር ቁጥር የሳፋሪኮም ኤምፔሳ ሠራተኞችን ጨምሮ ለማንም እንዳይሰጡ ወይም እንዳያሳዩ በጥብቅ ይመከራሉ።

**4.7.3** በኤምፔሳ ማውጫ በኩል የኤምፔሳን አገልግሎቶች እንዲሁም የዕቁብ አማራጭ ለሚጠቀሙ ተጠቃሚዎች የደንበኛ ድጋፍ አገልግሎትን ያቀርባል።

**4.7.4** በኤምፔሳ ሲስተም በኩል ኤሌክትሮኒክ ገንዘብ ክፍያ ሲፈጸምለት ወይም የዕቁብ አካውንቱ የአገልግሎት ጊዜው ሲያልፍ የደንበኛውን የዕቁብ/ኤምፔሳ አካውንት ኤሌክትሮኒክ ገንዘብ ተጠቅሞ ሒሳብ ይሞላል።

**4.8** ስምምነቱ ተፈጻሚ ከሚሆንበት ቀን ጀምሮ ስምምነቱ ተፈጻሚ ሆኖ እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ እርስዎን የሚከተሉትን ለማድረግ ተስማምተዋል፡-

**i.** በትዕዛዝ በሚደረግ ክፍያ የተጠራቀመውን ኤሌክትሮኒክ ገንዘብ ለመውሰድ ለሳፋሪኮም ኤምፔሳ ገንዘብ ወጪ የማድረጊያ ጥያቄ ያቀርባሉ።

**ii.** ሳፋሪኮም ኤምፔሳ የአገልግሎት ክ ፍያዎችን እና ኮሚሽኖችን ከኤምፔሳ አካውንቱ ላይ ለሰጠው አገልግሎት ቀንሶ እንዲያስቀር ፈቃድ ሰጥተዋል።

**iii.** በጽሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክ መንገድ ወይም በሌላ የተመረጠ ዘዴ ሳፋሪኮም ኤምፔሳ ማስታወቂያ ሲልክ ለአገልግሎቱ ሳፋሪኮም ኤምፔሳ የሚጠይቃቸውን የአገልግሎት ክፍያዎች ለመክፈል ተስማምተዋል።

**iv.** በመንግሥት ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቶች በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት ለመንግሥት መከፈል ያለባቸውን ማናቸውም ግብሮችና ሌሎች ክፍያዎች ለመክፈል ተስማምተዋል።

**4.9** ወጪ የሚደረጉ ገንዘቦች በቀጥታ በሲስተሙ በኩል ወይም በፈቃድ ሰጪው በኩል በትዕዛዝ እንደ ጥያቄ ሊቀርቡ ይችላሉ።

**4.9.1** ለደኅንነትና ለግልጽነት ሲባል አደራጁ ለክፍያ አፈጻጸም ሂደት የፈቃድ አሰጣጥ ደረጃውን እንዲወስን ይገደዳል።

**4.9.2** የተሰበሰበ ገንዘብ ተከፋይ ከሆነ በኋላ የዕቁብ አካውንት አባላት ኤሌክትሮኒክ ገንዘቡን ወጪ ማድረግ የሚችሉ ሲሆን ገንዘቡን በሚከተሉት አማራጮች በኩል ማግኘት የሚችሉ ሲሆን ሌሎች አማራጮችን ሳፋሪኮም ኤምፔሳ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊያስተዋውቅ ይችላል፡-

**i.** ኤምፔሳ ኤጀንት ጋር ሄዶ ገንዘቡን ወጪ ማድረግ

**ii.** የመርቻንት ክፍያ

**iii.** ወደ ራሳቸው ኤምፔሳ አካውንት ገንዘብን ማስተላለፍ፣ አገልግሎት ጊዜው ሲያልፍ እና እርስዎ ሲመረጡ የሚከናወነው ሂደት።

iv. ወደ ባንክ ሒሳብ ገንዘቡን ማስተላለፍ።

**4.10** የሒሳብ መግለጫ:- በዕቁብ አካውንቱ ላይ የተደረጉ የገንዘብ ዝውውሮችን በግልጽ በዝርዝር ማየት እንዲችሉ በእርስዎ የዕቁብ ማውጫ ላይ የቡድን የሒሳብ መግለጫን ማግኘት ይችላሉ። ከጊዜ ወደ ጊዜ በሳፋሪኮም ኤምፔሳ ለውጦች የሚደረግበት ይህ የሒሳብ መግለጫ የሚከተሉትን የሚይዝ ሲሆን ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ላይገደብ ይችላል:-

i. መዋጮ የተደረገበት ቀን እና ሰዓት

ii. መዋጮ ያደረገው ሰው ስም፣

iii. የመዋጮ ከፋዩ ስልክ ቁጥር (ተገቢነት ካለው)

iv. የኤምፔሳ ደረሰኝ (ወይም ማናቸውም አግባብነት ያለው ዋቢ ቁጥር)

v. ያለው ቀሪ ሒሳብ

## 5. የአገልግሎት ክፍያ

ሳፋሪኮም ኤምፔሳ በእያንዳንዱ ተከፋይ ክፍያ ከተከፋዩ ገንዘብ መጠን 0.5% የሚደርስ የአገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል (የአገልግሎት ክፍያ)። ይሁን እንጂ የአገልግሎት ክፍያው በአንድ ክፍያ ከ 500 ብር ሊበልጥ አይችልም።

## 6. የተጠያቂነት ገደብ

የሳፋሪኮም ኤምፔሳ ሚና የኤምፔሳ ዕቁብ አገልግሎት ተደራሽነትን ማረጋገጥና አገልግሎቱ በትክክል እንዲሠራ አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት ነው። በመሆኑም ሳፋሪኮም ኤምፔሳ በየተራ ዕጣ እንዲደርሳቸው ዕቁብ በሚጥሉ የቡድን አባላት መካከል ስለሚኖረው መዋጮ ኃላፊነቱን አይወስድም እንዲሁም መዋጮውንም አይከፍልም። ሳፋሪኮም ኤምፔሳ የቡድን አባላትን መረጃ አያጣራም፣ ቡድኖችን አይመረምርም ወይም ፈቃድ አይሰጥም፣ በቡድኖች ውስጥ ተሳትፎ አያደርግም፣ ወይም በቡድኑ ውስጥ ስለሚኖረው እንቅስቃሴ ምንም ዓይነት ተስፋ፣ ዋስትና ወይም ካሣ አይሰጥም። በማናቸውም ቡድን ውስጥ በሚኖርዎት ተሳትፎ ለሚደርስብዎት ማናቸውም ዓይነት ኪሣራ ወይም ጉዳት ሳፋሪኮም ኤምፔሳ ተጠያቂ እንደማይሆን ማወቅዎትን ያረጋግጣሉ። ሳፋሪኮም ኤምፔሳ ደንበኞን ሆነው በቡድኖች ተመራጭ እንደሆኑ አድርጎ ጥቆማ፣ ድጋፍ ወይም ምክር አይሰጥም። ለራስዎ ድርጊቶች ወይም ሳይፈጽሙ ለሚቀሩት ነገሮች በሙሉ ኃላፊነቱን እርስዎ ራስዎ እንደሚወስዱ ማወቅዎትን ያረጋግጣሉ። አባላት መዋጮዋቸውን በቡድን አደራጅ እና በአስተዳዳሪዎች በኩል ሳይከፍሉ በመቅረታቸው ለሚነሣ ማናቸውም አለመግባባት መፍትሔውን የማግኘት ኃላፊነት የእርስዎ የራስዎ እንደሆነ እንደሚያውቁ ያረጋግጣሉ።